በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ታቦት - ክፍል ፫
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ታህሳስ ፲፩ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.**



ታቦተ ጽዮን የምትገኝበት በእቴጌ መነን የተሠራችው የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን

# ኢትዮጵያ

- ኢትዮጵያ የሚለው መጠሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ 49 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡
- ኢትዮጵያ የሚለው ስም የተገኘው ጥንታውያን ግሪኮች የሀገራችንን ነዋሪዎች ይጠሩበት ከነበረው ስም ሲሆን ትርጉሙም በፀሐይ የጠቆረ ወይም የተቃጠለ ማለት ነው፡፡
- በ800 ዓ.ዓ. የኖረው ሆሜር የተባለው ግሪካዊ ገጣሚ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሲጽፍ ሰዎቹ ደጎች፣ ርኅሩሆች፣ እንግዳ ተቀባዮች፣ ጀግኖች መሆናቸውን ገልጧል፡፡
- ሰባውም ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ፅርዕ ቋንቋ ሲተረጉሙ ኩሽ የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ኢትዮጵያ ብለው ተክተው ተርጉመውታል፡፡ ይህም ከግብጽ ደቡባዊ ጠረፍ እስከ ሕንድ ያለውን ጥቁር ሕዝቦች የሚኖሩበትን ሀገር ያካትታል፡፡ "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።" *መዝ 67፡31፣ ኻል ነገሥት 19፡9፣ ኤር 13፡23፣ ኢሳ 43፡3፣ አስቴር 1፡1 …*
- ኢትዮጵያ የኩሽ ምድር ለመባል የበቃችው የካም የመጀመሪያ ልጅ የኩሽ ዘሮች ስለሰፈሩባት ነው፡፡ ይህቺ አገር በሌላ አጠራር የሳባ ምድር፣ አቢሲኒያ እየተባለችም ትጠራለች፡፡ ስያሜው የተገኘውም ከኩሽ ልጆች ከሳባና ከአቢስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በሳባ የሳባውያን ምድር በአቢስ ደግሞ አቢሲኒያ ተብላ ትጠራረ ነበር፡፡
- ዐረቦች ግን ምንጭ ባይኖራቸውም ድብልቅልቅ፣ ቅልቅል ለማለት ሐበሽ ብለው ይጠራሉ፡፡
- ቀድመው በሀገሪቱ ደጋማ ክፍል ይኖሩ የነበሩት የካምና የልጁ የኩሽ ዘሮች ሲሆኑ ቀስ በቀስ የሴም ዘር የሆኑ ነገዶች በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ ከየመንና ከአካባቢዋ ቄቀ ባሕርን እየተሻገሩ በሰሜናዊው የሀገሪቱ ክፍል መኖር ጀመሩ፡፡ በጽሑፍ ላይ የዋለውን የሀገራችንን ቋንቋ በተግባር ላይ አዋሉ፡፡ ከካም ዘሮችም ጋር በጋብቻ በመተሳሰር የአክሱምን መንግሥት መሠረቱ፡፡ ቀስ በቀስም መንግሥቱ እየተስፋፋ እየተጠናከረ ሄደ፡፡ የሳባ ቋንቋ እየተዳከመ ስለሄደ በግዕዝ ቋንቋ ተተካ፡፡
- ከይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አማርኛም የሕዝቡ ቋንቋ መሆን ጀመረ፡፡
- የጥንት ኢትዮጵያውያን በሳባ፣ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ግሪክም አገልግሎቱ ለዓለም አቀፋዊ ግኑኝነት ነበር፡፡

# የኦሪት እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት

- ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ እስከተነሳበት ዘመን ድረስ የነበረው የሕገ ልቦና የአንድ አምላክ እምነት ያለማቋረጥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በሴምና በካም ልጆችና የልጅ ልጆች ሲፈጸም ኖሯል፡፡ ኢትዮጵያዊቱ የሙሴስ ሚስትም ይህን አመላካች ናት፡፡ *ዘኍል 12፡1፡፡*

- የኦሪት እምነት በሀገራችን በይፋ ተቀባይነት በማግኘት የተሰበከው ከንግስተ ሳባ ዘመነ መንግግሥት ጀምሮ ነው፡፡

- በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንቡረ እድ ይስሐቅ የተጻፈው ክብረ ነገሥት በተባለው መጽሐፍ እንደተገለጸው ንጉሡ ሰሎሞን ለሚያሠራው ቤተ መቅደስ ሥራ የሚሆኑና ሌሎችንም ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በ520 ግመሎች ጭኖ በየጊዜው ለንግድ ወደ ኢየሩሳሌም ይኼድ የነበረው ታምሪን በየጊዜው ስለ ንጉሥ ሰሎሞን ጥበብ ለንግሥት ሳባ ይነግራት ነበር፡፡

- ኢትዮጵያዊቱ ንግሥትተ ሳባም ከአምላክ የተቸረውን የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብና ከፍተኛ የአስተዳደር ችሎታ በዓይኗ ለማየትና ጥበቡንም ቀስማ ዜጎችዋን በአግባብ ለማስተዳደር የሚያስችል ዕድል ለማግኘት ፈልጋ ዕውቀት ለመገብየት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች፡፡ "የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። ..." *ቀዳ ነገሥት 10፡1-13፡፡*

- ኢየሩሳሌምም በቆየችበት ወቅት እግዚአብሔር ለሰሎሞን ያደረገለትን ከተመለከተች በኋላ የኦሪትን እምነት ሙሉ በሙሉ ተቀበለች፡፡ ለስድስት ወርም ቆይታ ጸንሳ ስትመለስ ንጉሥ ሰሎሞን የጣት ቀለበቱንና ዴር ሡልጣን የተባለውን ቦታ በርስትነት ስጦታ አድርጎ ሰጣት፡፡ ዴር ሡልጣጠን እስከዛሬረ ድረስ ተከበሮ ይገኛል፡፡
- ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ በጉዞ ላይ እያለች አሥመራ አካባቢ ማይበላ ከተባለ ቦታ ከሰሎሞን የጸነሰችውን ልጅ ወለደችው፡፡ ስሙንም እብነ መለክ (የጥበበኛ ልጅ) ብላ ሰየመችው፡፡ ይህም ከጊዜ በኋላ ተለውጦ ምኒልክ ተባለ፡፡
- ከዚያም ጉዞዋን ቀጥላ መናገሻ ከተማዋ አክሱም ስትደርስ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ በደስታ፣ በሆታና በእልልታ ተቀበላት፡፡ የአዲስ ዓመትም ስጦታም ሰጧት፡፡ እንቁጣጣሽ የሚለውም ከዚሁ የመጣ ነው፡፡
- በሀገርዋም እውነተኛውን አምላክ በምልአት ማምለክ ጀመረች፡፡ ዜጎችዋም ይህንኑ እምነት ብቻ እንዲቀበሉ አደረገች፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስትና ሃይማኖት ወደ አገራችን እስከገባበት ጊዜ ድረስ የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ኖረ፡፡ *ካልዕ ነገሥት 9፡1-12፡፡*

# የታቦተ እግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ መግባት

- ቀዳማዊ ምኒልክ በ22 ዓመቱ አባቱ ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየት በታምሪን ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡

- ኢየሩሳሌምም ደርሶ ከአባቱ ጋር ከተገናኘ በኋላ በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ መምህርነት ሕገ ኦሪትን፣ ሕገ መንግሥትን… በሚገባ ለሦስት ዓመት ቆይቶ ተማረ፡፡

- ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰበት ወቅት በፈቃደ እግዚአብሔር ጥበብን በተሞላ መንገድ በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ የበኩር ልጅ በአዛርያስ አማካይነት ታቦተ ጽዮንም አብራ መጣች፡፡ በኢትዮጵያ የኦሪትን እምነት እንዲያስፋፉና የመንግሥትንም ተግባር በሚገባ ለማካሄድ እንዲረዱ ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተውጣጡ አሥራ ሁለት ሺህ የበኩር ወንድ ልጆችና ሌዋውያን ካህናት አብረው መጥተው ነበር፡፡

- ታቦቱንም ይዘው ሲሄዱ በጉዞአቸው ምንም መቅሰፍት አለመውረዱ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘላለም ለመባረክ የፈቀደው መሆኑን ተረድተው ሁሉም ደስ አላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ነው "የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ የምድያም አገር መጋረጃዎች ተንቀጠቀጡ። " *ዕንባቆም 3:7፡፡* "ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፥ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ፥ ቍርባኔን ያመጡልኛል።" *ሶፎንያስ 3:10፡፡* የተባለው፡፡

- በሐዲስም ለኢትዮጵያዊው "እነሆም፥ ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር" በማለት የተገለጸው እስከ ዘመነ ሐዲስ የኦሪት እምነትና ሥርዓት በኢትዮጵያ ጸንቶ መኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡

- ታቦተ ጽዮንም በዚህ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣች በኋላ በመጀመሪያ የተለየ ድንኳን በኋላም ቤተ መቅደስ (ምኩራብ) ተሠርቶላት ኖራለች፡፡ የምትገለገለውም ድንግላዊ በሆነ ገበዝ ነው፡፡ ማንም ሰው እንዲያያትም አይፈቀድም፡፡

- በኢትዮጵያ የኦሪት መሥዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ መሠዊያዎች እንደ ጣና ቂርቆስ ባሉ ገዳማት እስከ ዛሬ ድረስ ይገኛል፡፡

# ከአራቱ እምነታችን የተወረሱና እስከዛሬ ድረስ ያሉ ምልክቶቻችን

1. **የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር፡- ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ፡፡** "በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ።" ***ዘጸአት 25፡8፡፡***

2. **ታቦት፡- በንግሥተ ሳባ ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አክሱም ውስጥ በክብር አርፏል፡፡ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ በመጀመሪያ በጳጳስ ተባርኮና ሜሮን ተቀብበቶ ይቀደሳል፡፡ ታቦተ ሕጉም ይገባበታል፡፡** "ካህናቱም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት በቤቱ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከኪሩቤል ክንፍ በታች ወደ ነበረው ወደ ስፍራው አመጡት።" ***ቀዳ ነገ 8፡6፡፡***

3. **ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር፡፡** "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።" ***ዘጸአት 20፡8፡፡***

4. **የወንዶች ግዝረት፡-** "በእኔና በአንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ።" ***ዘፍጥ 17፡10፡፡***

5. **እንዳይበሉ የተከለከሉና የተፈቀዱ ምግቦች፡-** "ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በሉአቸው። ከምድር እንስሶች ሁሉ የምትበሉአቸው እነዚህ ናቸው። …" ***ዘሌዋውያን 11፡1-47፣ ዘዳግ 14፡3-21፡፡***

- **ንግሥተ አዜብ የተባለችው ንግስተ ሳባ ናት፡፡ በግዕዝ አዜብ ማለት ደቡብ ማለት ነው፡፡ ንግሥት ሳባ በኢየሩሳሌም ደቡብ በሚገኙ በኢትዮጵያና በየመን ገዝታለችና፡፡** ***ማቴ 12፡42፣ ሉቃ 11፡31፡፡***

- **የኦሪቱ እምነት እንደተጠበቀ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በቅዱስ ፊሊጶስ እጅ ተጠምቆ ክርስቲያን ሆኗል፡፡** ***የሐዋ ሥራ 8፡26-40፡፡***

- **ኢትዮጵያውያኑም ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐም ክርስትናን ተቀብለው የመጀመሪያውን ጳጳስ አባ ሰላማን ለማግኘት ያበቁን ሲሆኑ፣ ባለ አሥራ ሁለት መቅደስ የሆነችውን አሁን ፍርስራሹ የሚገኘውን የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንን አሳንጸዋል፡፡**

# ቤተ ክርስቲያናችን ከአብርሃ ወአጽብሃ እስከ ዛሬ

- አብርሃ ዋና ከተማውን አክሱም አድርጎ ሲገዛ አጽብሃ ደግሞ ዋና ከተማውን የረር አድርጎ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸዋል፡፡ ከነዚዘህም ውስጥ አክሱም ጽዮን፣ መርጦ ለማርያም፣ ተድባበ ማርያም፣ የካ ዋሻ ተክለሃይማኖት፣ የረር በዓታ/ሥላሴ ይጠቀሳሉ፡፡
- ከአባ ሰላማ በማስከተል ዘጠኙ ቅዱሳን ለክርስትና እምነት በኢትዮጵያ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የግዕዝ kንkን ቤተ ቀጢን በተባለው በአክሱም በሚገኘው ትምህርት ቤት ካጠኑ በ|ላ ብዙ መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል፡፡
- ቅዱስ ያሬድም ብዙ ፈተናዎች ቢገጥሙትም በእግዚአብሔር ፈቃድ በንጉሥ ገብረመስቀልም እገዛ ዛሬ በቤተክርስቲያናችን የምንገለገልበትን የመላዕክትን የምስጋና ዜማ ለቤተክርስቲያናችን አበርክቷል፡፡
- በአፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ የታቦተ ጽዮንን ወደ ኢትዮጵያ መግባት፣ የንግሥት ሳባንና የሌሎቹንም ነገሥታት ታሪክ የሚናገረው ክብረ ነገሥት፣ ታቦታትና፣ የኩርዓተ ርዕሱ ሥዕል በእንግሊዝ ጦር ጀነራል ናፒየር ተሰርቆ ከተወሰደ በ|ላ ክብረ ነገሥት በንጉስ ዮሐንስ አራተኛ ሲመለስ ሥዕሉና ታቦታቱ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይመለሱ ይገኛሉ፡፡
- በሐዲስ ቤተክርስቲያናችን ትምህርቱን በቃልም በተግባርም ጠብቃ እያስጠበቀች ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ በጌታችን ልደት፣ ጥምቀት፣ ስቅለት፣ ትንሳኤ፣ እና በዕለተ ሆሳዕና ወዘተ የሚፈጸሙት በመጽሐፍ የተጻፈልንን በተግባር የምናገኝበት ነው፡፡
- ቤተክርስቲያናችን በቅድስት አገርም ባሉአት ቅዱሳት መካናት ከጥንት የነበረ አገልግሎትዋን በዴር ሡልጣን፣ ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ገዳም፣ ዮርዳኖስ አጠገብ ያለው የሥላሴ ገዳም፣ ኢያሪኮ መቃረቢያ ያለው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ልሔም የሚገኘው ደብረ ሰላም ኢየሱስ፣ ቢታንያ ያለው የምስካበ ቅዱሳን ተክለሃይማኖት ገዳም … እየፈጸመች ትገኛለች፡፡
- ቤ/ክችን በመላው ዓለም ባሉአት አብያተ ክርስቲያናት ታቦታቱን በመንበሯ አድርጋ መንፈሳዊ አገልግሎትዋን በተለይ በዚህ ክፍለ ዘመን በመፈጸም ላይ ትተገኛለች፡፡ ይኸንም እስከ ዓለም ፍፃሜ በእግዚአብሔር ቸርነት ትቀጥላለች፡፡ *ማቴ 28፡19-20*፡፡ አምላካችን ቤ/ክችንን ይጠብቅልን፡፡ አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡